በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

# ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን

# 3. ምሥጢረ ቍርባን

- በቤተክርስቲያናችን የምሥጢራት ሁሉ መደምደሚያ ቅዱስ ቍርባን ነው፡፡ እያንዳንዱ ምሥጢረ ቤ/ክ ከተፈጸመልን በኋላ ቅዱስ ቍርባን እንቀበላለን፡፡

- ለምሳሌ ከጥምቀት እና ከሜሮን፣ ከክህነት፣ ከተክሊል፣ ከንስሓ… በኋላ በቀጥታ ሥጋ ወደሙን እንቀበላለን፡፡

- ቍርባን ማለት መባዕ፣ መሥዋዕት ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ ግን ቁርባን ብለን የምንጠራው ምስጢረ ቍርባንን የመሰረተው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መባዕ (መሥዋዕት) አድርጎ የሰጠንን ሥጋውንና ደሙን ነው፡፡

# ምሥጢረ ቍርባን…

- ‹‹… እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ፣ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም፡፡ ሥጋዬን የሚበላ፣ ደሜን የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው…›› ዮሐ 6፣53-56

- ‹‹ሲበሉም ኢየሱስ ሕብስቱን አንሥቶ ባረከ፣ ቆርሶም ለደቀመዛሙርቱ ሰጠና - ‹እንካችሁ ብሉ፣ ይህ ሥጋዬ ነው› አለ፡፡ ጽዋውንም አንሥቶ፣ አመስግኖ ሰጣቸው፤ እንዲህም አለ- ‹ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፣ ስለብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው› ›› (ማቴ 26፣26-28፤ ማር14፣22-25፤ 1ቆሮ 10፣16-17)

# ቅዱስ ቊርባን መታሰቢያ ነውን ?

- አንዳንድ ሰዎች ‹‹... ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህንን ለመታሰቢያዬ አድርጉት›› (ሉቃ 22፣19) የሚለውን መነሻ በማድረግ ‹‹ቊርባን መታሰቢያ ነው እንጂ እውነተኛ የጌታ ሥጋና ደም አይደለም›› ይላሉ፡፡

- ነገር ግን ጌታችን፡- ‹‹ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘላለም ህይወት አለው...›› አለ እንጂ ‹‹የሥጋዬን እና የደሜን መታሰቢያ›› አላለም (ዮሐ 6፣53)፡፡

- እንዲሁም ለሐዋርያቱ ሲሰጣቸው ‹‹ይህ... ሥጋዬ ነው››፣ ‹‹ይህ ... ደሜ ነው›› እያለ ሰጣቸው እንጂ ‹‹መታሰቢያ ነው›› አላላቸውም (ማቴ 26፣26፤ ማር14፣22-25፤ 1ቆሮ 10፣16-17)፡፡

# ቅዱስ ቊርባን መታሰቢያ ነውን ?...

- ነገር ግን ሥጋውና ደሙን ስንቀበል መከራውን ማለትም ለኛ ሲል መሰቀሉን፣ መሞቱን፣ መነሳቱን እንድናስብ ታዘናል። ይህም ቊርባንን መታሰቢያ ሊያሰኘው አይችልም (ሉቃ 22፣19፤ 1ቆሮ 11፣23-26)።

‹‹ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፣ ይህንንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና›› 1ቆሮ 11፣26

# በብሉይ ኪዳን የተገለጡ ዋናዋና የቅዱስ ቊርባን ምሳሌዎች

- መልከጼዴቅ ለአብርሃም ያቀረበው ህብስትና ወይን/ ሕብስተ-አኮቴት ጽዋዐ-በረከት (ዘፍ 14፣18፤ እብራውያን 7፣1-22)
- እስራኤል ከግብጽ ባርነት ነጻ ሲወጡ የሰዉት በግ/ ፋሲካ (ዘፀ 12፣3-6፤ 1ቆሮ 5፣7፤ ዮሐ 1፣29)
- ለእስራኤላውያን የወረደላቸው መና (ዘፀ 16፣14-15 መዝ 77፣24 ዮሐ 6፣32፣58)
- ሌዋዉያን ካህንት (በተለይም ሊቃነካህናቱ በዓመት አንድ ጊዜ) በቤተመቅደስ ለኃጢአት ስርየት መስዋእት አድርገው ያቀርቡት የነበረው የእንስሳት ደም (እብራውያን 9፣6-12፣22)

# በቤ/ክ የቅዱስ ቊርባን አፈጻጸም

- ዲያቆኑ ከንጹህ ስንዴና ከንጹህ የወይን ዛላ (ዘቢብ) የሚያዘጋጀውን ህብስትና ወይን ካህኑ በንጹህ ጻሕል እና በጽዋዕ አድርጎ በታቦቱ ላይ አስቀምጦ ስርአተ ቅዳሴ ያደርስበታል፡፡
- በዚህን ጊዜ ሕብስቱ ተለውጦ ሥጋ-መለኮት፣ ወይኑ ተለውጦ ደመ-መለኮት ይሆናል (ማቴ 26፣26-28፤ ማር 14፣22-25፤ ሉቃ 22፣17-20)፡፡
- ምስጢር የተባለውም፡ ሕብስቱ ወደ ሥጋነት፣ ወይኑ ወደ ደምነት ሲለወጥ ለማንም ስለማይታይ፣ እንዲሁም የተቀባዩ ኃጢአት ሲደመሰስ የምናስተውለው ስላልሆነ ነው፡፡
- በቤተክርስቲያናችን ለምእመናን የምናቀብለው ከሥጋውም፣ ከደሙም ነው (ዮሐ 6፣51-55)

# የቅዱስ ቊርባን አፈጻጸም…

- ቀድሰው ማቊረብ የሚችሉት ጳጳሳት እና ቀሳውስት ብቻ ሲሆኑ ሥጋውንና ደሙን መቀበል ያለባቸው ሁሉም ማለትም ከሕፃናት እስከ አረጋውያን ድረስ ያሉት ክርስቲያኖች ናቸው፡፡

- ነገር ግን ክርስቲያኖች በንስሓ ብቁ ሳይሆኑ (ሳይገባቸው) ቢቀበሉት ፍዳንና መቅሰፍትን ያመጣል (1ቆሮ 11፣27-32)፡-

- ‹‹ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋ እና ደም እዳ አለበት፡፡ ሰው ግን ራሱን ይፈትን፣ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ፣ ከጽዋውም ይጠጣ…››

# በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት

- ሥጋ ወደሙን ስንቀበል ቢያንስ ለ15 ሠዓታት ከምግብ እና ከመጠጥ እንድንርቅ ማለትም  እንድንጾም (ይህ ግን ከ7 ዓመት በታች ያሉ ሕፃናትን አይመለከትም)፣ የግል ንጽህናችንን እንድንጠብቅ  እና ከተቀበልንም በኋላ አድካሚ እንቅስቃሴ (ሥራ) ከማከናወን ወዘተ እንድንቆጠብ ሥርዓት ተሠርቷል።

- ማንኛውም ሰው ቅዱስ ቍርባን ከመቀበሉ በፊት ደም ከሰውነቱ ከፈሰሰው በዕለቱ እንዲቀበል አይፈቀድለትም። እንዲሁም አንዲት ሴት የወር አበባዋን በምታይበት ወቅት ቅዱስ ቍርባን እንድትቀበል አይፈቀድላትም።

# በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት…

- ባል እና ሚስት ሥጋና ደሙን ከመቀበላቸው በፊት፣ ለ3 ቀናት፣ ከተቀበሉ በኂላ ደግሞ ለ2 ቀናት ሩካቤ ሥጋ (ግንኙነት) ከመፈጸም እንዲታቀቡ ቤ/ክ ታስተምራለች፡፡

- ይህም ሩካቤ ሥጋ እንደ ነውር ተቆጥሮ ሳይሆን ለቅዱስ ቍርባን ክብር ለመስጠት ነው፡፡ (1ሳሙኤል 21፣5፤ ሉቃ 1፣23-24/ዘካርያስ ባለቤቱ ኤልሳቤጥን ያወቃት የቤተመቅደስ አገልግሎቱን ከፈጸመ ከ2 ቀናት በኂላ እንደሆነ ይተረካል፡፡)

- ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ካልሆነ በቀር በትዳር የሚኖሩ ባል እና ሚስት በተናጠል (ከሁለት አንዱ ብቻ) ቆራቢ እንዲሆኑ አይፈቀድላቸውም (ዮሐ 4፣ 15-16)፡፡

# መስብሃት ለእግዚአብሔር!